## ክፍል 3 ፓለቲካዊ መብቶችን ማክበር፤ የዜጎች መንግሥታቸውን የመለወጥ መብት፤

ሕገ መንግስቱና ሕጉ ዜጎች መንግሥታቸውን በሰላማዊ መንገድ የመለወጥ መብት እንዳላቸው እና ይህንኑ መብታቸውን በተግባር ነፃና እድሎ የሌለበት ምርጫ በማድረግ ይጠቀሙበታል ይላል። ይሁን እንጂ የተከሰቱ ስህተቶችና መራጮችንና የምርጫ ታዛቢዎችን ማስፈራራት የ2005ቱን ምርጫ ሂደት በብዙ ቦታዎች ያበላሹ ተግባሮች ነበሩ ገዥው ፓርቲ የኢህአዴግ ገዢ በመንግስቱ አሠራር ላይ የበላይነት በመንግሥ ነበረው።

መንግሥት በብሔር ብሔረሰቦች ፌዴሬሽን ላይ የነበረው ፖሊሲ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁሉም ዋና ዋና ብሔር ብሔረሰቦች እንዲወከሉ አስችሏቸዋል። ይሁን እና የአናሳ ብሄረሰብ ቡድኖች በሕግ አውጭው አካል ውስጥ ውክልና አላገኙም። በስድስት ክልላዊ መንግሥታት 23 ብሔረሰቦች በፓርላማው ውስጥ ወንበር ለማግኘት የሚያበቃ የሕዝብ ቁጥር አልነበራቸውም። ይሁን እንጂ በግንቦት 2005ቱ ምርጫ ከነዚህ ብሔሮች የተውጣጡ ግለሰቦች 547 መቀመጫዎች ባሉት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ላሉ 23 ልዩ መቀመጫዎች ተወዳድረው ነበር።

### ምርጫና የፖለቲካ ተሳትፎ

እንደ ሃገር ውስጥና የውጪ ታዛቢዎች ኢህአዴግ ከ547ቱ መቀመጫዎች 372ቱን ያሸነፈበት የግንቦት 2005ቱ ብሔራዊ ምርጫ ባጠቃላይ የሕዝቡን ፍላጎት ያሳየ ነበር። ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ያልተጠበቀ ጥንካሬ ያሳዩበትና በፓርላማ ያሉ ተወካዮቻቸው ቁጥር ከ12 ወደ 172 ያደገበት ነበር ።

መራጮችን እና የምርጫ ታዛቢዎችን ማስፈራራትን ጨምሮ የተለያዩ ስህተቶች በብዙ ቦታዎች ላይ የምርጫውን ሂደት አበላሽተውት ነበር ። መንግስትና ኢህአዴግም የ"መጨረሻ" ያሉትን የምርጫ ውጤት ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ከመግለፁ በፊት ገልፀው ነበር ። በተለይም በአማራ፤ኦሮሚያ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች ክልሎች ውስጥ ግድያዎች፤ መሰወሮች፤ የመራጭ ማስፈራራትና ማዋከብ እንዲሁም ሕገ ወጥ እስሮች በተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎች ላይ መድረሱን ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገው ነበር ። ( ክፍል 1 ሀን፤ለንና መን ይመለከቱ) የካርተር ማዕከል የታዛቢዎቹ ቡድን "የምርጫ ሳጥኖች ያለአግባብ መዘዋወር እንደነበረ፤ በስርዓቱ የተቀለሩ እንዳልነበረ ወይም የፓርቲ ሰዎች ከምርጫ ጣቢያዎች መታገድ እንደነበረ ወይም ሙሉውን የቆጠራ ሁኔታ እንዳይከታተሉ እንደተደረገ ማስረጃ አግኝቷል "በማለት ያለውን ስጋት ገልጿል ። በተጨማሪም " በምርጫው ዕለትና ከምርጫው በኋላ ማስፈራራትና ማዋከብ " እንደነበር ሪፖርት አድርጓል። የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች ልዑክ ሃላፊ ቅድመ ሪፖርት ባንዳንድ ቁልፍ ቦታዎች የተከሰቱ ችግሮችን በመጥቀስ እንደሚያመለክተው ከምርጫው በኋላ የነበረው ቅሬታ የማጣራት ሂደት " የአለም ዓቀፍ ደረጃን ያልጠበቀ ነበር " ብሏል ። እነዚህ ሁሉ ትችቶች ቢኖሩም ግን አለምዓቀፍ ታዛቢዎች ምርጫው አገሪቱ በምታደርገው የዴሞክራሲ ጉዞ ትልቅ እርምጃ እንደነበር ይናገራሉ ።

ምርጫውን ተከትሎ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የገዢው ፓርቲ መሣሪያ እንደሆነና በምርጫ ስላጋጠሙና በገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች ስለተደረጉ የምርጫ ኮሮጆን የመሙላት፤የቆጠራ ማጭበርበር፤ጉቦ፤ግድያዎች ፤ደብዳባዎችና ሰፊ የማስፈራራትና የማዋከብ ተግባራት ሲነገረው ምንም እርምጃ ባለመውሰዱ ከሰውታል።

በሰኔ 2005 በገዢው ፓርቲና በዋናዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በምርጫ ቅሬታዎች ላይ በተደረገው ድርድር ብዛት ያላቸውን የምርጫ ቅሬታዎች የሚፈታ አንድ ጊዜያዊ ሂደት እንዲፈጠር ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር ። እንደ ካርተር ማዕከል መግለጫ 44 የተለያዩ አጣሪ ኮሚቴዎች ባገሪቱ በ178 የምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ

ቅሬታዎችን አጣርተውና ተመልክተው ነበር ። የነዚህ ኮሚቴዎች ግኝትም የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በ31 ምርጫ ጣቢያዎች ድጋሚ ምርጫ እንዲያካሂድ ምክንያት ነበር ። በነዚህ የምርጫ ጣቢያዎች አዲሱ ምርጫ ተካሂዶ የነበረው በነሐሴ 2005 ነበር ።

በመስከረምና ጥቅምት 2005 መንግሥትና የተቃዋሚ መሪዎች ተቃዋሚዎች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ ተወያይተው ነበር ። አብዛኛው የሕብረት አባላት ፓርላማ ለመግባት ሲስማሙ አንዳንድ የቅንጅት አመራሮች በፌደራል ፓርላማ ውስጥ ሆነ በክልል ፓርላማዎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ፓርላማ እንደማይገቡ አስታውቁ ። ይሁን እንጂ ባመቱ መጨረሻ አብዛኛው የቅንጅት አባላት ፓርላማ ገብተው ነበር ። በጥቅምት መጨረሻ ቅንጅት ሕዝቡን ለሰላማዊ ተቃውሞ ጠርቶ ነበር ። በዚህ ተቃውሞ ሕዝቡ ጡሩንባ እንዲያሰማ፤ በኢህአዴግ ባለቤትነት ከሚተዳደሩ ንግዶች እንዳይገበያይ፤ እንዲሁም የመንግሥት ደጋፊዎችን ማግለል የመሣሠሉትን መንግሥት በግልፅ ሕገወጥ ያላቸውን ተግባራት እንዲያደርግ ቀስቅሰው ነበር ።

ከህዳር 1 ፤2005 ጀምሮ በተቃዋሚዎች ተደራጁ የተባሉ ፀረ-መንግሥት አመፆች አዲስ አበባ ውስጥ በመከሰታቸዉ መንግሥት በዛ ያሉ የተቃዋሚ አመራሮች እንዲሁም የነፃ ጋዜጣውን እና የሲቪል ማሕበረሰቡን አባላት በሕገ ወጥ ተግባራት ተሳትፈዋል በሚል በቁጥጥር ሥር አውሏቸው ነበር ። የፀጥታ ሃይሎች ከ30,000 እስከ 50,000 የሚደርሱ ተቃዋሚዎችን ያለ ክስ አስረው ነበር ።

የጦር ሰራዊቱ ጣልቃ ገብነትም በማንአለብኝነት ግድያዎችንና እስር የመሳሰሉ ሰፋ ያሉ የመብት ጥሰቶችን አስከትሎ ነበር ። የፀጥታ ሃይሎች ከ20ው የቅንጅት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ውስጥ የፓርቲውን ኘሬዚዳንት ሃይሉ ሻውልን፤ ምክትል ሊቀመንበሯን ብርቱካን ሚደግሳን፤ ዋና ፀሃፊውን ሙሉነህ ኢዮኤልንና ለአዲስ አበባ ከንቲባነት ተመርጠው የነበሩትን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ጨምሮ 12 አመራሮችን ባገር ክህደት፤በዘር ማጥፋት ሙከራ እንዲሁም በሌሎች ወንጀሎች ክስ በቁጥጥር ሥር አውለዋቸው ነበር።

(ክፍል 1ሠን ይመልከቱ)

ኢህአዴግ ጋር ግንኙነት ያላቸውና ደጋፊዎቹ የፌዴሬሽን ምክርቤትን 108 መቀመጫዎች በሙሉ ተቆጣጥረዋቸው ነበር ። የዚህ ምክር ቤት አባላት የሚሾሙት በክልል መንግሥታትና በፌደራል መንግሥት ነው ። ለአባላቱ የኢህአዴግ አባል መሆን ጥቅም ነበረው፡ ኢህአዴግ ብዙ ድርጅቶችን በባለቤትነት ያንቀሳቅስ ስለነበረ ለደጋፊዎቹ ሥራ ይሰጥ ነበርና ።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብዙ ቦታ የነበረው ተቃዋሚ ፓርቲ የቀድሞውን የቅንጅት አባላት አካቶ በአዲስ መልክ የተቋቋመው የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሲሆን 61 መቀመጫዎች ነበሩት ።

የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች በክልሎች ቢሮዎች ለመክፈት የክልል መንግሥታት ፈቃድ ማግኘት ነበረባቸው ። እንደ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ/ቅአዴፓ/፤ ሕብረትና ኦፌዴን ያሉ ፓርቲዎች ባመቱ ውስጥ የክልል መንግስታት ባለስልጣናት በአባሎቻቸው ላይ ያደርሱት የነበረው ማስፈራራትና ጥቃት ቀጥሎ እንደነበረ ተናግረው ነበር ። ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ጋዜጦች እንደዘገቡት ግድያዎችን፤ድብደባዎችን፤እስሮችን፤የቤት ቃጠሎዎችንና የንብረት ውርሶችን ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጉዳዮች ነበሩ ።

ባመቱ ውስጥ ባስልጣናት የተቃዋሚ አባላት ማዳበሪያ፣ ሌሎች የግብርና አገልግሎቶች የጤና ዕርዳታ ወይም ሌሎች በመንግሥት ሥር ያሉ ጥቅማጥቅሞች ማግኘት ከፈለጉ የተቃዋሚ አባልነታቸውን መተው እንዳለባቸው ይነግሯቸው እንደነበረ ሪፖርቶች ነበሩ ። ባለስልጣናት አብዛኛውን ጊዜ የተቃዋሚ ፖርቲዎችን ስብሰባዎች ይረብሹ ወይም ከሕግ ውጪ ያግዱ ነበር ። በ2003 መጨረሻና በ2004 መጀመሪያ ላይ ኢህአዴግ ስለዘጋው